ስፕሪንግ 2014

የተከበሩ የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ፡-

ለልጅዎ ጤና መጠበቅ ከፍተኛ ትኩረት እንሰጣለን። በኮሎምቢያ ዲስትሪክት በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች ከጤንነት ጋር ግንኙነት ባላቸው ልዩ ልዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ትምህርት ይሰጣል። ከነዚህ ጤና ነክ ርዕሶች ውስጥም ጤናማ አመጋገብ፤ የእዕምሮና የስሜት ጤንነት፤ አልኮል፣ ትምባሆና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆች፤ የበሽታ መከላከልና ፆታዊ ጤንነት የሚሉት ይገኙበታል። በ2010 በወጣው የጤናማ ትምህርት ቤቶች ድንጋጌ (The Healthy Schools Act of 2010) መሰረት፣ ከመዋለ-ህፃናት እስከ 8ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች የጤና ትምህረትን ማካተት ግዴታ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ(ሀይስኩል) ተማሪዎች ደግሞ ለመመረቅ በአንድ ሴሚስተር ውስጥ የጤና ትምህርት መማር አለባቸው። በእነዚህ ደረጃዎች ላይ የተማሪዎችን ውጤታማነት ለመመዘን፣ የዲሲ ሁሉን አቀፍ የምዘና ስርዓት(በእንግሊዝኛው መህፃረ ቃል DC CAS) ከሚሰጣቸው ፈተናዎች ውስጥ የጤናና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህረት ፈተና የሚካተት ይሆናል። ይህ ደረጃውን የጠበቀ ፈተና ለአምስተኛ ክፍል፣ ለስምንተኛ ክፍልና በ2013-2014 የትምህርት ዘመን በጤና ትምህረት ለተመዘገቡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚሰጥ ይሆናል።

በዲሲ የሚኖሩ ወጣቶች በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ በሚሄድ ውፍረት፣ በስኳር፣ በአስም፣ በአባለዘርዕ በሽታዎችና ያለ እድሜ እርግዝና ችግሮች እየተጎዱ የሚገኙ ሲሆን፣ የሚሰጠው ምዘናም ለተማሪዎቻችን ጤና እና ደህንነት ጠቃሚ የሆኑ በርካታ አርዕስቶችን የሚያካትት ነው። ሁሉም ከላይ በተጠቀሱት ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎች የሚሰጠውን ምዘና የሚወስዱ ቢሆንም፤ እንደ ተማሪዎች እድሜ የተዘጋጁትና ከፆታዊ ጤንነት ጋር የተያያዙት ጥያቄዎች ግን ለፈቃደኛ ተማሪዎች ብቻ ይሰጣሉ።

በጤና ትምህርቱ ውስጥ ከጾታዊ ጤና ጋር በተያያዘ የሚሰጡትን ጥያቄዎች በልጅዎ ፈተና ውስጥ እንዳይካተቱ ሊወስኑ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ከአጠቃላዩ የፈተና ጥያቄ ውስጥ በጣም ትንሽ ቁጥር ይኖራቸዋል። ልጅዎ እነዚህን ከጾታዊ ጤንነት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠየቁ **የማይፈልጉ** ከሆነ፣ ከዚህ በታች የቀረበውን ቅፅ ይሙሉ። **ከዚህ በታች የቀረበውን «አልፈቅድም» የሚለውን ሳጥን የሚመርጡ ከሆነ፣ ይህንን ቅፅ በመሙላትና በመፈረም በአስቸኳይ ለትምህርት ቤቱ ይመልሱ። ትምህርት ቤትዎ በመጀመሪያው የጤና ፈተና አስተዳደር ተሳታፊ ከሆነ ከማርች 31፣ 2014 በፊት፣ በሁለተኛው የጤና ፈተና አስተዳደር ተሳታፊ ከሆነ ደግሞ ከጁን 4፣ 2014 በፊት ቅጹ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል።** ተሳታፊ ላለመሆን መምረጥ በተማሪዎች ውጤት ወይም በCAS አሰራራቸው ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም። ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ሀሳብ ከአለዎት ለትምህርት ቤቱ ስልክ መደወል ይችላሉ።

ከሰላምታ ጋር፣

ሳንድራ ሽሊከር
በግዛቱ ተወካይ የትምህረት ተቆጣጣሪ

**የተማሪ ስም፡-** ______________________________

ትምህርት ቤት፡ ______________________________ ክፍል፡ ____________

[ ] አልፈቅድም፣ ልጄ ስለፆታዊ የጤና ትምህርት በሚቀርቡት ጥያቄዎች ላይ ተሳታፊ መሆን የለበትም።

የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ፡ ______________________________ ቀን: ____________

ስልክ ቁጥር: ______________________________